# እንደ ክርስቶስ አይነት አስተማሪነትን ማሻሻል—
# የግል ምዘና

እንደ አስተማሪዎች ተማሪዎች በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ እምነትን እንዲገነቡ እና የበለጠ እንደሱ እንዲሆኑ ለመርዳት በየጊዜው ጥንካሬያችንን እና ድክመታችንን መመዘን አለብን። ቀጣዩ ልምምድ የክርስቶስ ዓይነት አስተማሪነት መርሆችን እንድትተገብሩ ሊረዳችሁ ይችላል። እያንዳንዱ ቀጣዮቹ አረፍተ ነገሮች እንዴት እንደአስተማሪ እንደሚገልጿችሁ አስቡ። ለእያንዳንዱ አረፍተነገር ትክክለኛውን ምርጫ ምረጡ፤ (1) በጣም በጥቂቱ፣ (2) አንዳንድ ጊዜ፣ (3) አብዛኛውን ጊዜ፣ (4) ሁልጊዜ።

በመቀጠልም መንፈስ እንደመራችሁ ልታሻሽሏቸው የምትፈልጓቸውን ጥቂት ነገሮች በጸሎት ምረጡ። እቅድን አውጡ እንዲሁም እነዚህን መመሪያዎች ለመሻሻል እንዲረዷችሁ ተጠቀሙባቸው።

## በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ አተኩሩ

___ምንም ነገር እያስተማርኩ ቢሆን ስለኢየሱስ ክርስቶስ አስተምራለሁ።

___የኢየሱስ ክርስቶስን ምሳሌ እገላለሁ።

___ተማሪዎች በህይወታቸው የጌታን ፍቅር፣ ሀይል፣ እና ምህረት እንዲመለከቱ እረዳቸዋለሁ።

___ተማሪዎች ከሰማይ አባትና ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ያላቸውን ግንኙነት እንዲያጠነክሩ እረዳቸዋለሁ።

___ተማሪዎች የበለጠ ኢየሱስ ክርስቶስን ለመምሰል እያወቁ እንዲተጉ እረዳቸዋለሁ።

## የምታስተምሯቸውን ውደዱ

___ተማሪዎችን እግዚአብሄር በሚያያቸው መልኩ ለማየት እተጋለሁ።

___የማስተምራቸውን ለማወቅ—ያሉበትን ሁኔታ፣ ፍላጎታቸውን፣ እና ጥንካሬያቸውን ለመረዳት እሻለሁ።

___ለተማሪዎች በስማቸው እጸልያለሁ።

___ሁሉም የሚከበሩበት እና የሚያበረክቱት ነገር ዋጋ እንዳለው የሚያውቁበት ደህንነት ያለው ቦታ እፈጥራለሁ።

___ፍቅሬን ለመግለጽ ተገቢ መንገዶችን እፈልጋለሁ።

## በመንፈስ አስተምሩ።

___እራሴን ለማስተማር በመንፈሳዊ እዘጋጃለሁ።

___ተማሪዎቹ ስለሚያስፈልጋቸው ነገር መንፈሳዊ ሀሳቦችን ሳገኝ ምላሽ እሰጣለሁ።

___ተማሪዎች በመንፈስ ቅዱስ የሚማሩበትን ቦታ እና እድል እፈጥራለሁ።

___ተማሪዎች የግል ራእይን እንዲሹ፣ እንዲያውቁ፣ እና ተግባራዊ እርምጃ እንዲወስዱበት እረዳቸዋለሁ።

___አብዛኛውን ጊዜ ምስክርነቴን እሰጣለሁ፣ እናም ተማሪዎች ስሜታቸውን፣ ልምዳቸውን፣ እና ምስክርነታቸውን እንዲያካፍሉ አበረታታቸዋለሁ።

## አስተምሮቱን አስተምሩ።

___የእየሱስ ክርስቶስን አስተምሮ ለራሴ እማራለሁ።

___ከቅዱሳን መጻህፍትና  ከኋለኛው ቀን ነቢያት ቃሎች አስተምራለሁ ።

___ተማሪዎች ቅዱሳን መጻህፍትን እንዲሹ፣ እንዲያውቁ፣ ውስጡ ያሉትን እውነታዎች እንዲረዱ እረዳቸዋለሁ ።

___ወደመለወጥ በሚመሩ እና በኢየሱስ ክርስቶስ ላይ እምነትን በሚገነቡ እውነታዎች ላይ አተኩራለሁ ።

___ተማሪዎች ከኢየሱስ ክርስቶስ  አስተምሮ  ውስጥ ከነሱ ጋር የግል ዝምድና  ያለውን እንዲያገኙ እረዳቸዋለሁ ።

## በትጋት መማርን ጋብዙ

___ተማሪዎች ለትምህርታቸው ሀላፊነት እንዲወስዱ እረዳቸዋለሁ ።

___ተማሪዎች ወንጌሉን በየቀኑ በማጥናት አዳኙን ወደማወቅ እንዲመጡ አበረታታቸዋለሁ ።

___ተማሪዎች ለመማር እንዲዘጋጁ እጋብዛቸዋለሁ ።

___ተማሪዎች እየተማሯቸው ስላሉት እውነታዎች እንዲያጋሩ አበረታታቸዋለሁ ።

___ተማሪዎች እየተማሩት ያለውን እንዲኖሩ እጋብዛቸዋለሁ።